# How palliative care can help

**If you have an incurable or terminal illness, your local palliative care service can provide you and your family with support such as:**

1. A nurse calling you or visiting your home to see how you are going;
2. Help to manage any physical problems such as pain, so you are more comfortable;
3. Help to understand how some things might change – things such as taste, how much food you want to eat, your energy levels;
4. Talking to your family members if they are tired or distressed;
5. Help to talk to doctors and other health providers;
6. Help to understand all about your medications – what it is, what it does and when it should be taken;
7. Help to understand your options for treatment in Australia and helping you to choose what is best for you;
8. Arrange for you to have equipment to help you in your home, including a hospital bed, shower chair, wheelchairs etc. (a small cost may apply);
9. Arrange respite in the home for family and carers, so they have a chance to rest;
10. Help to understand where finanical help can be available, and how to access it;
11. Help to meet spiritual care needs and manage grief;
12. Help to find other services you may need.

# ከፓሌቲቭ ኬር አገልግሎት የምናገኛቸው ጥቅሞች

አንድ ሰው በጽኑ ታሞ መዳን የማይችልበት ደረጃ ሲደርስ ፓሌቲቭ ኬር እርስዎንም ሆነ ቤተሰብዎን በሚከተሉት መንገዶች መርዳት ይችላል።

1. አንድ ነርስ ለእርስዎ ተመድቦ ስልክ በመደወል ወይም እቤት ድረስ በመምጣት የሚያስፈልግዎትን ነገሮች ያወያዮታል ፤ ያሉበትንም ሁኔታ ያጤናል።
2. ያለብዎትን የጤና እክል በተለየም ህመምን በማስታገስ የተሻለ ጊዜ እንዲኖርዎት ያደርጋል።
3. በመጪው ጊዜ በጤናዎ ዙሪያ ሊመጡ የሚችሉ ለውጦችን ለምሳሌ የምግብ ቃና፤ምን ያህል ምግብ መብላት እንደሚችሉ፤ ከዚህም ሊያገኙ የሚችሉትን የሀይል መጠን እና የመሳሰሉትን የበለጠ እንዲገነዘቡ ያደርጋል።
4. ቤተሰብዎን በቅርበት በማነጋገር ድካም ወይም የጭንቀት ምልክት እንዳለባቸው ይከታተላል።
5. ሐኪሞችን እና ሌሎች የጤና ባለሞያዎችን ያነጋግርልዎታል።
6. ስለሚወሰዉዷቸው መድሀኒቶች በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያደርጋል።ለምሳሌ መድሀኒቱ ምንድን ነው፤ ለምን ይጠቅማል፤ መቼ መወሰድ አለበት።
7. በአውስትራሊያ ውስጥ ለህክምናዎ ያለዎትን አማራጮች እና ለእርስዎ የሚሆነውን ጥሩ አማራጭ እንዲያገኙ ያማክራል።
8. ለቤትዎ የሚሆኑ አንዳንድ መጠቀሚያዎችን ያዘጋጃል ለምሳሌ የሆስፒታል አልጋ፤ ገላ መታጠቢያ ወንበሮች፤ ተሽከርካሪ ወንበር ወዘተ (ለዚህ አገልግሎት የተወሰነ ክፍያ ሊኖረው ይችላል)።
9. የህመምተኛ ቤተሰቦችን ለተወሰነ ጊዜ በመተካት እረፍት እንዲገኙ ያደርጋል።
10. የገንዘብ እርዳታ ከየት እና እንዴት እንደሚገኝ ግንዛቤ እንዲኖርዎ ይረዳል።
11. መንፈሳዊ አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል። ሃዘንን መቋቋሚያ መንገዶችን ያመላክታል።
12. ሌሎች ጠቃሚ አገልግሎት የሚያገኙባቸውን መንገዶች ይጠቁማል።